<u>በነብዩ ኢሳያስ የተተነበየው የኢየሱስ አገልግሎት ኢሳ፡52፡13-53፡1-13</u>

<u>*መግቢያ*</u>*፡- የትንቢተ ኢሳያስ መጽሐፍ ከ2700 ዓመታት በፊት በነብዩ ኢሳያስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡ ኢየሱስ የተወለደው ከ2000 ዓመታት በፊት ነበር፡፡ ስለዚህ ት/ኢሳያስ ኢየሱስ ከመወለዱ 700 ዓመታት በፊት ተፃፈ፡፡ እ.አ.አ በ1950 ማለትም ከ60 ዓመታት በፊት ይህ ት/ኢሳያስ ሙሉ መጽሐፍ ከሌሎች ብዙ መጽሐፍት ጋር በእሥራኤል አገር በምድረ በዳ በሸክላ እንሥራ ውስጥ ተገኘ፡፡ መጽሐፉ የተፃፈው በቆዳ ላይ ሲሆን ኢየሱስ ከመወለዱ 300 ዓመታት በፊት በታሪክ ተመራማሪዎች እንደተፃፈ ይነገራል፡፡ይህ የኢሳያስ መጽሐፍ ቅጂ በአስገራሚ ሁኔታ ኢየሱስ ከመወለዱ ከ300 ዓመታት በፊት ተፃፈ፡፡ ቦታውም በእሥራኤል አገር በኢየሩሳሌም ከተማ ሊታይ ይችላል፡፡*

ኢሳ፡52፡13-53፡1-13 ‹‹አገልጋይ›› የሆነውን የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ያብራራል፡፡ ክፍሉን በጥንቃቄ አንብብና ከ700 ዓመታት በፊት የተተነበዩትን ነገሮች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካለው እውነት ጋር ለማገናኘት ሞክር፡፡ በኢየሱስ ሕይወት ላይ የተፈፀሙትን ሰፋ ያሉ እውነታዎች በአራቱ ወንጌላትና በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት መርምር፡፡

52፡13፡ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አለ፡፡
52፡14፡ ፊቱ ተጎሳቁሏል፣ በአለንጋ ተገርፏል፡፡
53፡3፡ በገዛ ሰዎቹ ተናቀ፡፡ የተጠላ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፡፡
53፡4፡ ብዙዎችን ፈወሰ፡፡ ደዌአቸውን ተሸከመ፡፡
53፡5፡ እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፣ስለበደላችንም ደቀቀ፡፡
53፡6፡ እግዚአብሔር የሁላችንም በደል በእርሱ ላይ ስላኖረ ሰላም አገኘን፡፡
53፡7፡ ተጨነቀ፣ተሰቃየም፡፡ በጽላጦስም ፊት አፉን አልከፈተም፡፡ ለሐጥአታችን እርሱ ተሰዋ፡፡
53፡8፡ ለመታረድ እንደሚነዳ በግ ዝም ብሎ መስቀሉን ተሸከመ፡፡
53፡9፡ ያለሐጥአቱ ከክፉዎች ጋር መቃብሩን አደረጉ፡፡ የአርማቴው ዮሴፍ ከተባለው ባለጠጋ ጋር መቃብሩ ሆነ፡፡
53፡11፡ ትንሣኤ ሆነ፡፡ ስለእኔ ሐጥአት አርሱ በመሰዋቱ በትንሣኤው ሃይል እኔ ከገሃኔምና ከሐጥአት ነፃ ወጥቻለሁ፡፡
53፡12፡ እሱ ስለ አመጸኞች ስለተሰቃየ በሰማይ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አለ፡፡
53፡13፡ በሰማይ ሆኖ ይማልድልኛል፡፡

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ከዚህ ክፍል ስለ ኢየሱስ የምማረው አዲስ ነገር ምንድነው?
2. በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስን ወድጄና ፈቅጄ እንዳመልከው የበለጠ የሚያነሳሳኝ የትኛው ክፍል ነው?
3. ኢየሱስ ወድጄ ለመከተልና ለማገልገል የምፈልገው አምላክ ነውን?
4. የት/ኢሳያስ መጽሐፍ ከ700 ዓመታት በፊት መፃፉና ኢየሱስ ከመወለዱ ከ300 ዓመታት በፊት ከምድር የመገኘቱ እውኔታ እንዴት እምነቴን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳደርግ ያደርገኛል?
5. ኢየሱስ አገልጋይ ሆኖ ተገልጧል፡፡ አሁን የኢሳያስን መጽሐፍ ስላጠናህ ‹‹አገልጋይ›› የሚለው ላንተ ምን የተለየ ትርጉም ይሰጣል?
6. በቤትህ፣በቤተሰብህና በሥራህ ቦታ እንዴት እንደ አገልጋይ መሆን ትችላለህ?

**<u>መግቢያ፡-</u>** ከሆስፒታሉ ተልዕኮ አንዱ ላልዳኑት ወንጌልን መመስከር ነው፡፡ ይህ ለአንተ ምን ማለት ነው?

2ቆሮ፡5 አንብብ፡፡

1. ወንጌል የምንመሰክርባቸው ምክንያቶች ምንድናቸው? እነዚህን ምክንያቶች በቁ፣1,9,10,14,15,18,19,20 ዘርዝርና ተወያይ፡፡

2. በቁ፣18, 19, 20 ላይ እግዚአብሔር ተልዕኮ ሰጥቶናል፡፡ እኛ የእሱ አምባሳደሮች (የወንጌል መልዕክተኞች) ነን፡፡ ይህ ማንን ነው የሚያሳየው? የወንጌል መመስከር ሥራ ለወንጌላዊያን ብቻ የተሰጠ ነውን?

3. በዚህ 2ቆሮ፣5 ላይ አንተ ምን እንድትሆን ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው?

## <u>የእግዚአብሔር ልብ ያረፈበት ሠራተኛ ምን ዓይነት ነው? ቲቶ፣2፡9-10</u>

<u>ቲቶ፣2፡9-10</u> ‹‹ስለ መድኃኒታችን ስለ እግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት በሁሉ ያመስግኑ ዘንድ ባሪያዎች ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ በሁሉም ደስ እንዲያሰኙ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ ምከራቸው›› ይላል፡፡

<u>መግቢያ፡-</u> በዚህ ክፍል ያሉ መመሪያዎች ዛሬ ለእኛ ለሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል ሠራተኞች የሚያስተምሩት እውነት አለ፡፡ ክፍሉን እንደገና በጥንቃቄ አንብብ፡፡ እግዚአብሔርን የሚመስል ሠራተኛ ምን ዓይነት ነው?

1. ለቀጠረህ ድርጅት ወይም ለአለቃህ ተገዛ ማለት ምን ማለት ነው? አመለካከትህና ተግባርህ ምን መሆን አለበት ትላለህ? ለቀጠረህ ድርጅት ወይም ለአለቃህ ለመታዘዝ ወሰን ወይም ገደብ አለው?

2. አለቆቻችንን ማስደሰት ማለት ምን ማለት ነው? በሥራ ላይ ያለህ አመለካከት ምንድነው?

3. አለቆቻችንን አለመቃወም ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ሰው በውስጡ ያለውን መጥፎ አመለካከት በንግግሩ እንዴት ይገለጻል? በአለቃህ ላይ ታጉረመርማለህ? አለቃህን ትተቻለህ? ወይስ አክብሮት አታሳይም? እነዚህን የመሳሰሉ አመለካከቶችን እግዚአብሔር እንዴት ያያል? በሥራ ላይ ስለሚገጥሙ ጉዳዮች (ችግሮች) ከቀጣሪ ጋር መወያየት የሚቻልበት ትክክለኛው መንገድ ምንድነው?

4. መስረቅ ምንድነው? ይህ ምናልባት ግልጽ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ይህ ችግር እንዴት ሊከሰት እንደሚችል በሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል ውስጥ ተወያዩ፡፡ ሆስፒታሉ እንደ ሳሙና፣መጽሐፎችና ሌሎች አላቂ ዕቃዎች ያሉ ብዙ ንብረቶች ስላሉትና አንተ ስላስፈለገህ ከሆስፒታሉ ንብሬት መውሰድ ተገቢ ነውን? ሰዎች ለምን የሚሰርቁ ይመስልሃል?

5. ታማኝ መሆን ማለት ምን እንደሆነ ተወያዩ፡፡ በጊዜ በመምጣትና ሥራህን በትክክል በመሥራትህ ታማኝ ነህ? በክርስቲያን ሆስፒታል ውስጥ ስለምትሠራው ሥራ እግዚአብሔር ምን ይላል?

6. እግዚአብሔርን የሚመስል ሠራተኞች መሆን ያስፈለገው ለምንድነው? እኛ ጥሩ ሠራተኞች ከሆንን በእኛ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር የሚመጣው ማነው?

<u>የቃል ጥናት፡-</u> ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን በትጋት አድርጉት ቆላ፣3፡23

**<u>የእግዚአብሔር ልብ ያረፈበት ሠራተኛ በሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል ውስጥ ምን ይመስላል</u>**

**<u>*መግቢያ*፡-</u>** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በቲቶ፣ 2 ላይ ለሠራተኞች የተሰጡትን አራት ትዕዛዛትን ተወያይተን ነበር። በዚህ ሳምንት ደግሞ ጥሩ ሥራ ከምን የመነጨ እንደሆነና እግዚአብሔር ጥሩ ሥራ ስለማይሠሩ ሠራተኞች ምን እንደሚል እንወያያለን።

ቲቶ፣2፡9-14 አንብብ።

1. እግዚአብሔር ለአማኞች ፀጋን ሰጥቷል። ፀጋው ምን እንድናደርግ ያስተምረናል ቁ፣12

2. ኢየሱስ ዳግመኛ ይመጣል። ይህ የተባረከ ተስፋችን ነው። እኛ ምን ዓይነት ሕይወት እንድንኖርለት ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው ቁ፣12 እና 14 ተመልከት። ይህ ተስፋ በሥራችን ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድነው?

3. ምሳ፣10፡26 18፡9 21፡25 አንብብና ተወያይ። ስለ ሰነፍ ሠራተኛ እግዚአብሔር ምን ይላል?

4. ምሳ፣31፡13 የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳርፍ ሠራተኛ ምን ዓይነት ነው?

5. ከዚህ ጥናት የተነሣ እግዚአብሔር እንዴት እንድትለወጥ ይፈልጋል?

<u>የቃል ጥናት፡-</u> ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን በትጋት አድርጉት ቆላ፣3፡23

**አንደኛ ሣምንት የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳርፍ አለቃ ምን ይመስላል? ቆላ፣3:22-4:1**

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት የእግዚአብሔርን ልብ ስለሚያሳርፉ ሠራተኞች ተምረን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ የእግዚአብሔርን ልብ ስለሚያሳርፉ አለቆች (ቀጣሪዎች) እንማራለን፡፡ እግዚአብሔር ለልጆቹ ሁሉ መመሪያ አለው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር የራሱን ቤተክርስቲያን ከዓለም ልዩ እንድትሆን ስለሚፈልግ ነው፡፡ በተቀደሰው አኗኗር እንድንኖር እግዚአብሔር እኛን መመሪያዎችን ያስተምረናል፡፡

የውይይት ጥያቄዎች ቆላ፣3:22-4:1 አንብብ

1. ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር ለእኛ ሥራ ሰጥቶናል፡፡ ቀጣሪዎችና ሠራተኞች እንዴት መሥራት አለባቸው? ክርስቲያን ሠራተኞች ለማንነው የሚሠሩት?
2. ለእግዚአብሔር ብለን ብንሠራ ምን እንቀበላለን?
3. እግዚአብሔር ቀጣሪውንና ሠራተኛውን እንዴት እንደሚያይ ከዚህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን? በቀጣሪውና በሠራተኛው መካከል ስላለው ግንኙነት ይህ ክፍል ምን አስተዋጽኦ ያበረክታል?
4. ቀጣሪዎች ተጠያቂ የሚሆኑት ለማን ነው?
5. ቀጣሪዎች ሠራተኞችን እንዴት መቀበል (ማስተዳደር) አለባቸው? ቆላ፣4:1 አንብብ፡፡ ለምን ቆላ፡4:1 አንብብ፡፡
6. ‹‹በጽድቅና በቅንነት›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

1ጴጥ፣2:11-18 አንብብና ተወያዩ፡፡

1. ለባለሥልጣናት የምንገዛው ለምንድነው?
2. አንድ ባለሥልጣን የሚያጠፉትን ለመቅጣትና ትክክለኛ ሥራ የሚሠሩትን ለማመስገን ስልጣን አለው፡፡ አንድ ባለስልጣን ስልጣኑን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንዳለበት ተወያዩ፡፡
3. እያንዳንዱ ሰው በመልካም ሕይወት መኖር የሚያስፈልገው ለምንድነው?
4. የአንድ ክርስቲያን አለቃ ባሕሪ መመዘኛዎች ምንድናቸው?

1ጢሞ፣2:1-3 አንብብ

1. ለባለስልጣናት መፀለይ ያለብን ለምንድነው? ለዚህ ውጤቱ ምንድነው?
2. ከዚህ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሣምንት ማድረግ ያለብህ ምንድነው?

## <u>ሁለተኛ ሣምንት ፣የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳርፉ ሠራተኞች</u>

<u>**መግቢያ**</u>፡- ባለፈው ሣምንት እግዚአብሔር ለማንም ፊት አይቶ እንደማያዳላ ተምረን ነበር፡፡ ቀጣሪዎችና ሠራተኞች እርስ በርስ በመከባበር እንዲኖሩና ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሠሩ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡

1. ዘዳ፣24፡14-15 አንብብ፡፡ ሠራተኞች ምን እንዲያደርጉ ነው እግዚአብሔር የሚያዝዘው? በወር ሁለት ጊዜ የሚከፍሉ ቀጣሪዎች ይህንን እንዴት ተግባራዊ ያደርጋሉ?

2. ያዕቆ፣5፡1-6 አንብብ፡፡ የሠራተኞቻቸውን ደመወዝ በሥርዓት የማይከፍሉ ወይም የሚቀሙ ቀጣሪዎች ምን ይሆናሉ? የሠራተኞችን ጩኸት ማን ይሰማል? ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?

የሚከተሉትን ጥቅሶች ከምሳሌ መጽሐፍ አንብብና የመልካም መሪ ወይም ቀጣሪ መመዘኛዎች ምን እንደሆኑ ተወያይ፡፡

1. ምሳ፣8፡34-36 የሚፀልይና እግዚአብሔርን የሚያዳምጥ

2. ምሳ፣11፡1 እና 3 ታማኝ የሆነ

3. ምሳ፣12፡24 ታታሪ ሠራተኛ

4. ምሳ፣13፡18 ተግሳጽን የሚቀበል

5. ምሳ፣15፡1 እና 18 የለዘበ (በቁጣ ያልሆነ)መልስ የሚሰጥና እና ትዕግስተኛ የሆነ

6. ምሳ፣15፡22 ብዙ ምክርን የሚሰማ

7. ምሳ፣29፡4 በጽድቅ (በአግባቡ) የሚፈርድና ጉቦ የማይቀበል

8. ምሳ፣29፡19 ሌሎችን እንዴት ደቀመዝሙር ማድረግ እንዳለበት የሚያውቅ

1ጢሞ፣2፡1-3 ለባለሥልጣናት እንድንፀልይ ያሳስበናል፡፡ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የባሕሪ መመዘኛዎች አንዱን ወስደህ ለሆስፒታሉ መሪዎች ፀልይ፡፡